ባሕረ ሀሳብ ዘቅዱስ ዲሜጥሮስ

ጌታቸው በቀለ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራሷና ከመላው ዓለም ልዩ የሚያደርጋት አንዱ የዘመን አቆጣጠሯ ነው :: ዘመንን ለመቁጠር የሚያገለግለው ትምህርት ባሕረ ሐሳብ፣ መርሐ ዕውር፣ ሐሳበ ብርሃን፣ መጽሐፈ ሐሳብ በሚል ስያሜ ይታወቃል::

የዘመን አቆጣጠር ስለ ማኅበራዊ ኑሮ ጠቀሜታና የሃይማኖት ተግባሮችን ለማከናወን የሚረዳ፣ የዘመኖችን ሒደት የሚያስቃኝ የኅብረተሰብ ጉዳዮችን በሥነ ሥርዓት ለማራመድ፣ የሕዝብና የሃይማኖት በዓላትን ለማወቅ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው:: ለዚህም ነው የአቡሻኽር ሊቃውንት ባሕረ ሐሳብን ሁሉ ሰው ሊማረው ይገባል የሚሉት:: በባሕረ ሐሳብ ትምህርት ያለፉት ዓመታትን፣ አሁን ያለንበትን ዘመንም ሆነ ወደፊት እስከ ዘመነ ምዕአት የሚመጡትን ዓመታት በቀመር እያሰላን በየዘመኑ አጽዋማት የሚገቡበትን በዓላት የሚውሉበትን ማወቅ እንችላለን::
_N¬WÃN yzmN xöÈ-R

ጥንታውያን የዘመን አቆጣጠርን ስንመለከት ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ቀን መቁጠርና ማስላት የተጀመረው አዳም ከገነት ከወጣና ተስፋውን ከሰማ ጊዜ ጀምሮ ነው:: አዳምም ሰባት ዓመት ትእዛዙን ጠብቆ በሕጉ ጸንቶ ከቆየ በኋላ ምክረ ከይሲን ሰምቶ ከፈጣሪው ጋር ተጣልቶ ከገነት ወጣ:: በኋላ አዳም ንስሐ ቢገባ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሰጠው:: ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ብሎ ተስፋውን ነገረው:: አዳምም ለልጆቹ ይህን ተስፋ ነገራቸው::

ልጆቹም እኩሌቹ በጨርቃ እኩሌቹ በከዋክብት እንዲሁም በፀሐይ ዘመናትን ሲቆጥሩ ኑረዋል::የዘመን ቁጥርም የተጀመረው በዚህ ምክንያት ነው:: ነቢያትም ትንቢት ሲናገሩ ሱባኤ ሴቆጥሩ ኖረዋል:: የሰው ልጆች የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል ዘንግተው በእጃቸው የሠሯቸው ጣዖታትን ያመልኩ ነበር:: ተስፋውን ከሚጠባበቁ በስተቀር የቀጠሮውን ቀን ከ 5500 ዘመን ጀምሮ ያለውን ቁጥር የሚያስብ ወደታች የሚቆጥር የነቢያትን ሱባዔ የሚመረምር ሕዝብ ጠ ፋ:: ጨረቃን የሚያመልከው በጨረቃ ሲቆጥር፣ ከዋክብትን የሚያመልከው በከዋክብት ሲቆጥር ነበር:: ለዘመን መቁጠሪያ የተሰጡት መጋብያነ ዕለታት ፀሐይ፣ ጨረቃንና ከዋክብትን አማልክት አደረጋቸው:: ፈላስፎችና የሥነ ፈለክ ተመራማሪዎች ደግም ለዚህ ድርጊት ዋነኞች ነበሩ:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ ዘመናትን ይቆጥሩ ነበር::

እነዚህ ጥንታውያን አቆጣጠሮች የሚባሉት የአይሁድ ፣ የግብጻውያን፣ የዩልዮስ ቄሣርና የሩቅ ምሥራቅ ዘመን አቆጣጠሮች ናቸው:: አይሁድ ዘመንን የሚቆጥሩት የፀሐይንና ጨረቃን የተከተለ ሲሆን ሁለቱንም ለማጣጣም ይሞክራል:: ይህ አቆጣጠር 30 ቀናት ካሉት ከባለ 12ቱ የፀሐይ ወር በ11 ቀኖች ያንሳል::

ግብጻውያንም ቀደም ብሎ በጨረቃ በኋላ ደግሞ በፀሐይ መቁጠር ጀምረዋል:: 30 ቀናት ያላቸው 12 ወራት ለአንድ ዓመት መቁጠሪያ ይጠቀማሉ:: አምስት ትርፏን ጨምረው በአጠቃላይ 365 ቀንን አንድ ዓመት ማለት ጀመሩ:: ይህን አቆጣጠር የጁሊየስ ቄሣር ዘመን ድረስ ይጠቀሙበት ነበር:: አሁን ግን የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስተያን ብቻ ዓመቱን ትሠፍርበታለች::

የጁሊየስ ቄሣር ዘመን አቆጣጠርንም ስንመለከት 365 ቀናት ያሉትን የአሌክሳንድርያ ዘመን አቆጣጠር አብነት በማድረግ የጳጉሜን አምስት ቀን እየበተነ በሌሎቹ ላይ በመጨመር ይቆጥራሉ:: 30 ቀን የሆነውን የካቲት /ፍጽበረጭፈረየ/ 28 አድርጐ መስከረም፣ ኅዳር፣ ሚያዝያ፣ ሰኔ 30 ቀናት እንዲኖራቸው ሌሎቹ ጥቅምት፣ ታኅሣስ፣ጥር፣ መጋቢት፣ ግንቦት፣ ሐምሌና ነሐሴ 31 ቀናት ሆኖ የካቲት ወር በአራት ዓመት አንድ ጊዜ በእኛ ዘመን /ልጽፈጥ ይጽፈረ/ 29 እየሆነች በሌሎቹ ደግሞ 28 ቀናት ይዛ እንድትኖር አደረገ::

በዚህም ሮማውያኑ 12ቱን ወር በ365 ቀን ወይም በ366 ቀን ሲያጠናቅቁ አንድ ዓመት ይላሉ:: እኛና ግብጻውያን ግን 12ቱ ወር ላይ አንድ ባለ አምስት ወይም ስድስት ቀን በመጨመር በእኩል ቀን ብዛት ግን በሚለያዩ ወሮች አንድ ዓመት እንላለን:: ከዚህ በላይ ያየናቸውን አቆጣጠሮች ስናያቸው የአረማውያንና ሌሎች የሚጠቀሙባቸው ናቸው:: የቀናቱ ፣የወራቱ፣የዓመታቱ ስያሜያቸው ብቻ ሳይሆን ልዩነታቸው ከአምልኮተ እግዚአብሔርም የራቁ ሆነው እናገኛቸዋለን::

yzmN xöÈ-RN yqmrW ¥nW)

የዘመን አቆጣጠርን የቀመረው 12ኛው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ድሜጥሮስ ነው። ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እስከ ድሜጥሮስ ዘመን ድረስ ክርስቲያኖች ሁዳዴን በየ ዓመቱ ሁልጊዜ ከጥምቀት ማግስት / ከጥር 11 ቀን/ ጀምረው እስከ የካቲት 21 ቀን ድረስ ዓርባ ቀን ከጾሙ በኋላ ጥቂት ቀኖች ቆይተው የሕማማትን ሳምንትና የትንሣኤውን በዓል ሲያከብሩ ቅዱስ ድሜጥሮስ አየ። የቀድሞዎቹ ሰዎች እንደዚህ ያደርጉ የነበረው የአጽዋማቱንና የበዓላቱን መንስኤ / ጥንት/ ለማግኘት ሲፈልጉ የቀኖቹን መግቢያና በዓላቱ የሚውሉበትን ፈልገው በደረሱበት ቀን ለማዋል ነበር። አስልተው / ለበዓል መዋያም ሆነ ለጾም መግቢያ/ የሚያገኙት ዕለተ እሑድ ወይም በሌሎች ቀናት ቢሆን በዚያ ዕለት ያከብሩታል እንጂ እኛ ዛሬ እንደምናደርገው ለውጠው / ከሳምንቱ ዕለታት/ የተወሰኑ ቀኖች አይሰጧቸውም ነበር። ይህ ቅዱስ ድሜጥሮስን ያሳስበው ነበር።

QÇS D»_éS _Nt ng„ XNdMN nW b!l#)

yD»_éS ySÑ TRÙ» l!”WNt$ XNdÃTt$T D»_éS ¥lT mS¬wT ¥lT nWÝÝ bmS¬wT k ›Yn g#DF k_RS XDF XNÄ!Ãw-#bT Xs#M yx{ê¥TN yb›§TN x!y›RG x!YwRÄcWN -NQö {ÐLÂÝÝ xNDM D»_éS ¥lT ÍÂ ¥lT nWÝÝ ÍÂ ¼mB‰T¼ Yø kb@T bgb# g!z@ kö_ ytsqlW k¥jT ytN-l-lWN XNÄ!ÃúY Xs#M yx{ê¥T½ yb›§TN x!y›RG x!YwRD bGL{ ÃúÃLÝÝ xNDM D»_éS ¥lT gÖÄÂ ¥lT nWÝÝ bgÖÄÂ ÿì kb@T XNÄ!dRs# Xs#M yx{ê¥T yb›§T x!y›RG x!YwRÄcWN -NQö Y{ÍLÂÝÝ xNDM D»_éS ¥lT t‰‰ ¥lT nW¿ kt‰‰ §Y bw-# g!z@ MNŒ GÅW XNÄ!¬Y Xs#M yx{ê¥T yb›§T x!y›RG x!YwRÄcWN ÃúÃLÝÝ**

ድሜጥሮስ አባቱ አርማስቆስ ይባላል። ደማስቆ የሚባል አጐት ነበረው። ለአጐቱ ልዕልተ ወይን የምትባል አንዲት ሴት ልጅ ነበረችው። አጐቱ በሚሞትበት ጊዜ ለአባቱ አደራ ሰጥቷት ሞተ።ከድሜጥሮስ ጋር አፈር ሲፈጩ ውሃ ሲራጩ በአንድነት አደጉ። አካለ መጠን ሲያደርሱ እናጋባቸው ብለው መከሩ። ሕግ ይጽናላቸው ንብረት ይፈጸምላቸው ብለው ነውን ? ዘመዳሞቹንስ እናጋባቸው ብለው ነውን? አይደለም። ምእመናን ያነሱት አሸካራ የበዛበት፣ ትምህርት ያልሰፋበት ወራት ነበርና ነው።ደግሞም ከአሕዛብ ከመጋባቱ ከክርስቲያን መጋባቱ ይሻላል ብለው ነው እንጂ። አንድም ተዘምዶተ ነፍስ ሲፈርስ ተዘምዶተ ሥጋ ይፍረስ ብለው ነው። መክረውም አልቀሩ አጋቧቸው። ከዚህ በኋላ አዝማደ መርዓዊ ወመርዓት ተሰብስበው ከጫጉላ ቤት አግብተው መጋረጃ ጥለው ሕግ ይፈጽሙ ብለው ጥለዋቸው ሄዱ/ወጡ/።

በዚህ ጊዜ አስቀድማ ወንድሜ ያንተ ወንድምነት የኔ እህትነት ይቅር ብለህ ነው? አለችው። እሱም ፈቃዴ ሆኖ አይደለም የእናት የአባት ፈቃድ ማፍረስ ይሆናል ብዬ ነው እንጂ አላት። እንኪያስ ፈቃድህ ካልሆነ እንተወው አለችው። ደግ ነው እንተወው፣ ስለተውነው ግን አንለያይ። ልጅ ባንወልድ መሀን ሆኑ ይሉናል እንጂ አልተጋቡም አይሉንም። የተለያየን እንደሆነ ግን አንችንም ከአሕዛብ ወገን እኔንም ከአሕዛብ ወገን ያጋቡናል አላት። በዚህ አንድ ሆነው ተስማምተውና ተባብረው አንድ ምንጣፍ አንጥፈው፣ አንድ ልብስ ለብሰው በአንድ አልጋ እየተኙ 48 ዘመን ኖረዋል።

መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ሌሊት ቀኝ ክንፉን ለእርሱ ግራ ክንፉን ለእርሷ አልብሷቸው አድሮ ሲነጋ በመስኮት ወጥቶ ሲሄድ በአምሳለ ፀዓዳ ርግብ ይታይ ነበር። የድሜጥሮስ ኑሮው እርፍ አርቆ ሞፈር ጠርቦ ወይን አፅጽቆ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ከተክል ቦታው ቢገባ በጥቅምት ከተከላት ወይን አንዲት የወይን ዘለላ ያለ ጊዜዋ አብባ አፍርታ አገኛት። ይህችንስ እኔ ልመገባት አይገባኝም ብሎ ወስዶ ለሚስቱ ሰጣት። እሷም ይህችንስ እኛ ልንመገባት አይገባንም ብላ በመሶበ ወርቅ አድርገህ ወስደህ ከሊቀ ጳጳሱ በረከት ተቀብለህባት ና አለችው። በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የሚመሩ ናቸውና ቃላቸው አንድ ሆነ።

ዐሥራ አንደኛው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ቶልያኖስ ይባል ነበር። እሱም አርጅቶ የሚሞትበት ጊዜ ደረሰ። ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ መጥቶ አንተ አረጀህ የምትሞትበትም ጊዜ ደረሰ በወንበርህ የሚተካ እንድታገኝ አንተም እዘን ሕዝቡም ይዘኑ አለው።

ከዚህ በኋላ ሕዝቡን የራቀውን በጦማር የቀረበውን በአዋጅ ሰብስቦ እኔ አረጀሁ የምሞትበት ጊዜ ደረሰ። በወንበሩ የሚተካ እንድታገኙ እናንተም እዘኑ እኔም አዝናሁ ። እናንተም ወደ እግዚአብሔር አመልክቱ እኔም ወደ እግዚአብሔር አመለክታለሁ ብሎ ቀን ቀጥሮ ሰደዳቸው። ወደ እግዚአብሔር

ቢያመለክት የታዘዘ መልአክ መጥቶ ያለጊዜዋ ያፈራች አንዲት የወይን ዘለላ በረከት አገኛለሁ ብሎ በመሶበ ወርቅ አድርጌ ይዞልህ የሚመጣ ሰው አለ። ካንተ ቀጥሎ የሚሾመው እርሱ ነው ብሎታል። በቀጠሯቸው ቀን ሕዝቡ ተሰብስበው መጡ። እንደምን ሆናችሁ አገኛችሁ አላቸው። እንደምን ያለ ሰው አገኘህልን አሉት? ያለጊዜዋ ያፈራች አንዲት የወይን ዘለላ በረከት አገኛለሁ ብሎ በመሶበ ወርቅ አድርጌ ይዞልኝ የሚመጣ ሰው አለ። ከእኔ ቀጥሎ የሚሾመው እርሱ ነው ብሏቸዋል።

በበነጋው ጉባዔ ሠርቶ ሲያስተምራቸው ከቀድሞው ይልቅ ዘገየባቸው አባታችን ምነው ከቀድሞው ይልቅ ዘገየህብን አሉት፣ ያልኩት ሰው እስኪመጣልኝ ድረስ ነው አላቸው። ከዚህ በኋላ ድሜጥሮም ሲመጣ አሻግሮ አይቶ ያ ያልኳችሁ ሰው መጣ። ከእኔ ቀጥሎ የሚሾመው እርሱ ነውና ቢሆን በውድ ባይሆን በግድ እንዳትለቁት አላቸው። ምነው አስቀድሞ ነገራቸው በፊት ባልነገራቸው ነበር ቢሉ ቅዱሳን ክብራቸውን በሰው ፊት ቢገልጹባው አይወዱምና ስለዚህ ነው።

ድሜጥሮስም በደረሰ ጊዜ እጅ ነስቶ ቆመ። ሊቀ ጳጳሱ ቶልዮስም የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንዴት አለህ አለው። እግዚአብሔር ይመስገን ብሎ ወይኑን አበረከተ። ቶልዮስም ድሜጥሮስን ባርኮት ቀድሶት አልዋለም አላደረም ዕለቱን ወርፎአል። ድሜጥሮስም ቶልዮስን ቀብሮ ዕለቱን ልሂድ ብሎ ተነሣ። ሕዝቡም አባታችን የተማረ እኔ ያልተማርኩ፣ አባታችን ድንግል ንጹሕ እኔ ሕጋዊ በዚያውስ ላይ እንደምን አድርጌ ይሆንልኛል። የተማረ ግብረ ገብ ያለው መርጣችሁ ሹሙ እንጂ አላቸው ። እነርሱም አባታችን ነግሮናል የአባታችን ቃል አይታበልም፤ ሲሆን በውድ ሳይሆን በግድ አንለቅህም አሉት።

ከዚህ በኋላ እንዳልለቀቁት አይቶ ምን ሥርዓት አድርሶ ነው የሚሾመው አላቸው። አንቀጸ አባግዕን በቃሉ አንብቦ ተርጉሞ ነው አሉት። ከቤተመዛግብት መጽሐፍን አምጡልኝ አለ። ከዚያ ቀድሞ እንኳንስ ትርጓሜውን ንባቡን አያውቅም ነበር። መጽሐፉን እስኪያመጡለት ድረስ በቃለ አንብቦ ተርጉሞ ተሹሟል። ይህም ብቻ አይደለም ከዚህ አያይዞ ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ተገልጾለታል። በሀገራቸው ሊቀ ጳጳስ በተሾመ ገዜ ሰባት ቀን ቀድሶ ያቆርባቸዋል። ድሜጥሮስም በልደት፣ በጥምቀት፣ በትንሣኤ ቀድሶ በሚያቆርብበት ጊዜ ሄዶ ከደጀ ሰላም ይቀመጣል። ሕዝቡ ለመቁረብ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ የሕዝቡ ኃጢአት በብርሌ ካለ ጠጅ እንደገባ ሣር ሆኖ የሕዝቡ ኃጠ ያትና ጽድቅ እየታየው አንተ በቅተሃል ግባ አንተ አልበቃህም አትግባ። አንተ ዛሬ ይገባሃል ግባ። አንተ አይገባህም አትግባ እያለ ይመሰክርና ይከለክላቸው ነበር።

ሕዝቡም እጨጌነት ከሚስት እንዲሉ እርሱስ እንኳ የማይገባውን ሚስቱን ይዞ በአባታችን በቅዱስ ማርቆስ ወንበር ተቀምጦ የእኛን ኃጢአት በምን አውቆት ነው የሚከለክለን? እያሉ ያሙት ጀመር። ከዚህ በኋላ ሕዝቡ በሐሜት የሚጎዳ ሲሆን የታዘዘ መልአክ መጥቶ /ኦ ድሜጥሮስ ኢትፍቱ አድኅኖ ርእስከ ለባህቲትከ ክስት ሎሙ ምስጢረ ዘሀሎ ማዕከሌከ ወማዕከለ ብእሲትከ፤ ድሜጥሮስ ሆይ ሕዝቡ በአንተ ምክንያት በሐሜት ተጐዱ ራስህን ብቻ ማዳን አትውደድ በአንተና በሚስትህ መካከል ያለውን ምስጢር ግለጥላቸው።/ አለው። ከነገራቸው ሁሉ ቅዱሳን ክብራቸው በሰው ፊት ቢገለጽባቸው አይወዱምና ውዳሴ ከንቱ ይሆንብኛል ብሎ ነው እንጂ ፈቃደ እግዚአብሔር ከሆነማ እሺ በጐ ብሎ ሕዝቡን ያራቀውን በጦማር የቀረበውን በአዋጅ እንጨት እየያዛችሁ ተሰብሰቡ አለ። ሕዝቡም እንጨት እየያዙ ተሰበሰቡ።

ከቅዳሴ ሲገባ በደጀ ሰላሙ አጠገብ እንደ መስቀል ደመራ አስደምሮ እሳቱን አስነድዶ ሊቀድስ ገባ። ከቅዳሴ ሲወጣ ልብሰ ተክህኖውን ማዕጠንተ ወርቁን ይዞ ዕጣን ወግሮ ኦ አምላክ ዘለዓለም ቀዳሚ ወደኃሪ ዘአልብከ ጥንት ወኢተፍጻሜት እያለ እሳቱን ሦስት ጊዜ ዞሮ በመካከሉ ገብቶ እንደውሃ ይዋኝ ጀመር። ሚስቱንም ልዕልተ ወይን ብሎ ጠርቶ /ንዒ እኅትየ ስፍሒ አዕፈኪ ወንስኢ ፍሕመ። ብሎ/ ከፍሕሙ በእጁ እየታፈነ በልብሷ አስታቅፎ እሱ ወንድ ሆኖ በልማደ አዳም እኔ ሴት ሆኜ በልማደ ሔዋን እንደማንተዋወቅ ምስክራችን ይህ ነው እያልሽ ሕዝቡን ሦስት ጊዜ ዙረሽ እጅ ነስተሽ አፍስሺው አላት። እሷም እሺ ብላ እሱ ወንድ ሆኖ በልማደ አዳም፣ እኔ ሴት ሆኜ በልማደ ሔዋን እንዳንተዋወቅ ምስክራችን ይህ ነው እያለች ሕዝቡን ሦስት ጊዜ ዞራ እጅ ነስታ ብታፈስሰው እንኳን ሰውነቷን ሊፈጃት ከለበሰችው ልብስ ከዘሀው ከማጉ አንድ ስንኳ አልጠቆረም፣ አልቀነበረም። እሱም ከእሳቱ መካከል ቆሞ ሲጸልይ ስንኳን ሰውነቱን ሊፈጀው ከለበሰው ልብስ ከዘሀው ከማጉ አንዱ ስንኳ አልጠቆረም፣ አልቀነበረም።ይ ኸውም በዚህ ዓለም አንድ ልብስ ለብሰው አንድ ምንጣፍ አንጥፈው በአንድ አልጋ እየተኙ ሲኖሩ ርስሐተ ኃጢአት እንዳላገኛቸው ንጽሐ ጠባይዕ እንዳላደፈባቸው ያጠይቃል።

ከዚህ በኋላ ሕዝቡ አባታችን ሳናውቅ አምተንሃል ብለው ወድቀው ማረን አሉት። ይቅር ስለ እግዚአብሔር አላቸው። ይቅር ካልከንስ ናዝዘህ ኃጢአታችንን አስተስርይልን አሉት። ይፍታሕ ወይሕድግ ያንጽሕ ወይቀድስ ካህን ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ብሎ ናዘዛቸው። እንዲህ ብሎ በናዘዛቸው ጊዜ በሰውነታቸው ያለ ኃጢአት እንደ ሽማ እንደ መጐናጸፊያ ተጠቅልሎ በፊታቸው ሲወድቅ አይተውታል። ከዚህ በኋላ የእርሱ ሊቀ ጳጳስነት ፀና። እርሷም ከማኅበረ ደናግል ተቆጠረች።
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአቡኻሽር መምህራን እንደሚያስተምሩት አጽዋማትና በዓላት ጥንታቸውን እንዲጠብቁ ይመኝ የነበረው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ድሜጥሮስ፤ በዓላትና አጽዋማት በጥንቱ ተራክቦአቸው የሚውለበትን ጊዜ ለማስተካከል ይህን የሚወስን የቁጥር ሕግ ለማግኘት ተመኘ። ነነዌ፣ በዓተ ጸም/ ዐቢይ ጾም/፣ ጾመ ሐዋርያት ከሰኞ፤ ደብረዘይት፣ ሆሣዕና፣ ትንሣኤና ጰራቅሊጦስ ከእሑድ፤ ርክበ ካህናት፣ ጾመ ድኅነት ከረቡዕ፣ ስቅለት ከዓርብ ዕርገት ከሐሙስ ባይወጡ ባይናወጡ እያለ ይመኝ ነበር። ለጌታ የተመኙትን መግለጽ ልማዱ ነውና የታዘዘ መልአክ መጥቶ ድሜጥሮስ ሆይ ይህ ሁሉ በሀሳብ ይፈጸማልን ቢፈጽሙት ቢያደርጉት ነው እንጂ ሱባኤ ግባ ብሎ አዘዘው። ቅዱስ ድሜጥሮስም ሱባኤ ገባ ከቀኑ /ከመዓልቱ/ ሰባት ሱባኤ ከሌሊቱ 23 ሱባኤ ገባ።

ስለምን የሌሊቱን ሱባኤ አብዝቶ የቀኑን / የመዓልቱን / አሳነሰው ቢሉ ቀን የተጣላ ሊያስታርቅ፣ የታመመ ሲጠይቅ፣ የሞተ ሲቀብር ይውላል። ሌሊት ግን ከዚህ ሁሉ ነፃ ነውና የሌሊቱን ሱባኤ አበዛው። ከቀኑ ሰባት ሱባኤ በሰባት አባዝቶ 49 ሲሆንለት፤ 49 አቡነ ዘበሰማያት ይደግማል ሠላሳውን አንድ ወር ብሎ በዐውደ ወርኀ ቢያኖሩ / በ30 ገድፎ ወይም አካፍሎ/ 19 ይተርፋል። ይህ መጥቅዕ ይሁንህ ብሎታል። ጥንተ መጥቅዕ የተባለም ይህ ነው። ከሌሊቱ 23 ሱባኤ ደግሞ በሰባት አባዝቶ 161 ዕለት ይሆናል። 161 አቡነ ዘበሰማያት ይደግም ነበር። ከዚህ 150ውን አምስት ወር ብሎ በዐውደ ወርኀ ቢያኖሩ /በ30 ገድፎ / 11 ይተርፋል። አበቅቴ ይሁንህ ብሎታል። ጥንተ አበቅቴ የተባለ ይህ ነው። መጥቅዕ ለቀን አበቅቴ ለሌሊት ማውጫ ያገለግላሉ።

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ድሜጥሮስ የአጽዋማትና የበዓላት ኢየዓርግና አይወርድ ተገልጾለት አጽዋማቱ ከሰኞ እንዳይወጡ መግቢያ ሥርዓት ሠራላቸው። ለበዓላቱ ደግሞ ደብረዘይት፣ ሆሣዕና፣ ትንሣኤ፣ ጰራቅሊጦስ ከእሑድ፤ ስቅለት ከዓርብ፤ ርክበ ካህናት፣ ጾመ ድኅነት ከረቡዕ፤ ዕርገት ከሐሙስ እንዳይወጡ አደረገ። የሕማማትን ሳምንትና የትንሣኤን በዓልም ከጾመ ዓርባ አያይዘው እንዲያከብሩ ሥርዓት ሠራላቸው። በተጨማሪም በዓመቱ ውስጥ ከወሰነላቸው ጊዜ ወደታች እንዳይወርዱ ወደላይም እንዳይወጡ የቀመር ሕግ አወጣ።

የአጽዋማትና በዓላት ኢይወርድ/ከዚህ በላይ አይወጣም/ ወኢየዓርግ /ከዚህ በታች አይወርድም/እንደሚከተለው ነው።

የነነዌ	ኢይወርድ	ጥር	17	ኢየዓርግ	የካቲት	21
የዐቢይ	ጾም	ኢይወርድ	የካቲት	1	ኢየዓርግ	መጋቢት	5
የደብረ	ዘይት	ኢይወርድ	የካቲት	28	ኢየዓርግ	ሚያዝያ	2
የሆሣዕና	ኢይወርድ	መጋቢት	19	ኢየዓርግ	ሚያዝያ	23
የስቅለት	ኢይወርድ	መጋቢት	24	ኢየዓርግ	ሚያዝያ	28
የትንሣኤ	ኢይወርድ	መጋቢት	26	ኢየዓርግ	ሚያዝያ	30
የርክበ	ካህናት	ኢይወርድ	ሚያዝያ	20	ኢየዓርግ	ግንቦት	24
የዕርገት	ኢይወርድ	ግንቦት	5	ኢየዓርግ	ሰኔ	9
የጰራቅሊጦስ	ኢይወርድ	ግንቦት	15	ኢየዓርግ	ሰኔ19
የጾመ	ሐዋርያት	ኢይወርድ	ግንቦት	16	ኢየዓርግ	ሰኔ	20
የጾመ ድኅነት ኢይወርድ ግንቦት 18 ኢየዓርግ ሰኔ 22							

እነዚህን በሰባት አዕዋዳት ዐውዶ በሶርያ፣ በአንጾኪያ፣ በሮም ላሉት ለሦስቱ ሊቀነ ጳጳሳት አራተኛ በኢየሩሳሌም ላለው ኤጲስ ቆጶስ ጽፎ ሰደደላቸው ። እነርሱም ተቀብለው ሐዋርያት በዲድስቅልያ ካስተማሩት ጋር አንድ ሆኖ ቢያገኙት ደስ ብሎአቸው ተቀብለው ባሕረ ሐሳቡን አስተምረውታል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንም ተቀብላ በሥራ ላይ አውላዋለች። እንዲያውም ባሕረ ሐሳብን ሁሉም ሰው ሊማረው የሚገባ መሆኑን በአጽንኦት ታስተምራለች። ባሕረ ሐሳብን የተማረ ሰው ከሀገሩ ተሰዶ አሕዛብ ሀገር ቢሄድ እንኳን ጾም አይገድፍም በዓል አይሽርም፤

ምክንያቱም አጽዋማት የሚገቡበትን በዓላት የሚውለበትን ተምሯልና። ባሕረ ሐሳብን ያልተማረ ካህን ካህን መሆን አይገባውም በማለት ያስተምራሉ።

ቤተ ክርስቲያንም በአዲስ ዘመን መባቻ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በተገኙበት በዓላት የሚውሉበት አጽዋማት የሚያዙበትን አይዓርግ ኢይወርዳቸውን በባሕረ ሐሳብ እያሰላች ለምእመናን ታውጃለች።

ሰባቱ አዕዋዳት

ዐውደ ዕለት፡ - ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያሉት 7ቱ ዕለታት ናቸው። እሊህ አውራኅን /ወሮችን/ ለማስገኘት በ7 በ7 ሲመላለሱ ይኖራሉ።

ዐውደ ወርኀ፡ በፀሐይ ዘወትር 30 ቀን ነው። በጨረቃ አንድ ጊዜ 29 አንድ ጊዜ 30 /ዕለት/ ነው። በፀሐይ ግን ዘወትር 30 /ዕለት/ ነው። እሊህም ዓመታትን ለማስገኘት በ30 በ30 ሲመላለሱ ይኖራሉ።

ዐውደ ዓመት፡ በጨረቃ 354 ዕለት ከ22 ኬክሮስ ነው። በፀሐይ 365 ዕለት ከ 15 ኬክሮስ ነው።

ዐውደ አበቅቴ /ንዑስ ቀመር/፡ 19 ዓመት ነው። በዚህም ፀሐይና ጨረቃ መንገዳቸውን ፈጽመው በተፈጠሩበት ጐኅት /መስኮት/ ተራክቦ /ግንኙነት/ ያደርጉበታል። ይህም ቀናቸውን እኩል ይጀምራሉ ማለት አይደለም።

ዐውደ ፀሐይ፡ 28 ዘመን ነው። አንድ ዐውደ ፀሐይ 19 ጊዜ ሲመላለስ አንድ ዐቢይ ቀመር ይሆናል።/19 ×28= 532/ በዚህም ዕለትና ወንጌላዊ ይገናኙበታል። ዕለቱ ረቡዕ ወንጌላዊው ማቴዎስ ነው። በየ 28 ዓመት ዕለቱ ረቡዕ ወንጌላዊው ማቴዎስ ነው።

ዐውደ ማኅተም /ማዕከላዊ ቀመር/፡ 76 ዓመት ነው። ዐውደ ማኅተም ሰባት ጊዜ ሲመላለስ አንድ ዐቢይ ቀመር ይሆናል። /7×76=532/ በዚህም ወንጌላዊና አበቅቴ ይገናኙበታል። ወንጌላዊው ዮሐንስ አበቅቴው 18 ነው። ጥንቱ ለቀመር ዕለተ ሠሉስ ወወንጌላዊ ማቴዎስ ወፍጻሜሁ ዕለተ ሰኑይ ወወንጌላዊ ዮሐንስ /የቀመር መነሻው ማክሰኞ ዕለት ወንጌላዊው ማቴዎስ ሆኖ፣ መጨረሻው ሰኞ ዕለትና ወንጌላዊው ዮሐንስ ነው/እንዲል።

ዐውደ ቀመር / ዐቢይ ቀመር/፡ 532 ዘመን /ዓመት/ ነው። በዚህም ዕለት፣ ወንጌላዊው አልቦ /ዜሮ/ አበቅቴ እነዚህ ሦስቱ ይገናኙበታል። ዕለቱ ሠሉስ / ማክሰኞ/ ወንጌላዊው ማቴዎስ አበቅቴው አልቦ /ዜሮ/ ነው።

የባሕረ ሐሳብ አወጣጥ

የባሕረ ሐሳብን አወጣጥ ለመረዳት ያስችለን ዘንድ ከዚህ በታች ያሉትን መሠርታዊ ነገሮች ማወቅ ያስፈልጋል።

1 **ዓመተ ፍዳ** /ዓመተ ኩነኔ/፡

ዓለም ከተፈጠረ አንስቶ እስከ ልደተ ክርስቶስ ያለው 5500 ዘመን፤ ዘመነ ብሉይ፣ ዓመተ ፍዳ፣ ዓመተ ኩነኔ ይባላል። ዓመተ ፍዳ የተባለው ከአዳም ተፈጥሮ ጀምሮ እስከ ልደተ ክርስቶስ ወይም እስከ ዘመነ ሥጋዌ የነበረው 5500 ዘመን ነው። የሰው ልጅ በአዳም ውድቀት ምክንያት በባርነት በሰይጣን ቁራኝነት በሥጋ ድካም የነበረው 5500 ዘመን ነው። ይህም እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ በሥራው ተጠያቂ ሆኖ ፍዳውን የሚቀበልበት፣ የቅጣት ዕዳውን የሚከፍልበት ዘመን በመሆኑ ዓመተ ፍዳ ተብሏል። ሮሜ 3:11-20 :: የሐዋ 13:39።

ይህ ዘመን አምስት ቀን ተኩል ይባላል። የ5500 ዘመን ትንቢታዊ አባበል አምስት ቀን ተኩል ተብሎ ሲነገር የሚገኝበት መንገድ መኖሩ ይታወቃል። ሊቁ ቀሌምንጦስ እንደተናገረው በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ፤ በአምስት ቀን ተኩል ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ እንደተባለ። የዚህ አባባል መነሻው ከምን የመነጨ ነው? ቢሉ አንድ ሺህ ዓመት

አንድ ቀን ተብሎ ከተጻፈው ከመጽሐፍ ቅዱስ ዘይቤ ጋር አንድ ነው ። እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ።እንዲል። 2ኛ ጴጥ 3:8። ዘፍ 14:34። መዝ 89/90/: 4።

አንድን ሺህ ዓመት አንድ ቀን እያለ አምስቱን ሺህ ዓመት አምስት ቀን በማለት አምስት መቶውን/የሺውን አጋማሽ/ እኩል ቀኑን ደግሞ /መንፈቀ ዕለት/ በማለት መምህራኑ ይገልጻሉ።

2 ዓመተ ምሕረት:

ከልደተ ክርስቶስ ወዲህ ያለው ዘመን ዓመተ ምሕረት፣ ዓመተ ሥጋዌ፣ ዘመነ ሐዲስ ይባላል። ይህም ሰው በምሕረትና በአምላካዊ ቸርነት የሚኖርበት የጸጋ ዘመን ዘመነ ብሥራት፣ ዘመነ ወንጌል በመሆኑ ነው። ገላ 4:1- 7። ማር 1:14-15።

ዓመተ ምሕረት ትንቢት ተነግሮላት ሱባኤ ተቆጥሮላት በቀጠሮ ስትጠበቅ የቆየች ናት እንጂ፤ እንደ አጋጣሚ የደረሰች እንግዳ ዘመን አይደለችም ኤር31:34። ምሳ 23:5-6 ። ዳን 9:24-26። በነቢዩ ኢሳይያስ የተመረጠችውን የእግዚአብሔር ዓመት አስብ ተብሎ መነገሩ ይታወሳል። ኢሳ 61:2 ሉቃ 4:17-19። ዳግመኛም በተመረጠች በተወደደች ዕለት ሰማሁህ በመድኃኒትም ቀን ረዳሁህ እንደተባለ። ኢሳ 49:8። 55:3-6 2ኛ ቆሮ 6:2 ኤር 31:31-34። የክርስቶስ ልደት ለዓመተ ፍዳ ለዓመተ ኩነኔ ማክተሚያ መደምደሚያ ለዓመተ ምሕረት ግን መጀመሪያ ነው።

3. ዓመተ ዓለም

መላው የዓመተ ኩነኔና የዓመተ ምሕረት ድምር ዓመተ ዓለም ይባላል። ከጌታ ልደት በፊት የነበረው ዓመተ ፍዳ 5500 እና እስከ አሁን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ያለው 1999 ዓ.ም. ዘመን ተደምሮ ነው። መላው 7499 ዓ.ም ይሆናል። ዓመተ ዓለም ባለው ዓመተ ምሕረት የሚል አብነት ይገኛል። ስለምን ዓመተ ዓለምን ዓመተ ምሕረት አለው ቢሉ ሰው በዚህ ዓለም ሳለ ኃጢአት ሠርቶ ንስሐ ቢገባ ምግባር ቢሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረት ይቅርታ የሚያገኝበት ስለሆነ ዓመተ ዓለምን ዓመተ ምሕረት አለው። በተመረጠችው ዕለት እሰማሃለሁ በመዳኛ ዕለትም እረዳሃለሁ። ዛሬ የተመረጠች ዕለት ናት። ዛሬ የመዳኛ ዕለት ናት። እንዲል። ኢሳ 49:8።

ወንጌላዊ:

ወንጌላዊውን /ዘመኑን/ ለማወቅ ዓመተ ኩነኔን 5500 እና ዓመተ ምሕረት/አሁን ያለንበትን/ በመደመር ውጤቱን ለአራቱ ወንጌላውያን /ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ/ በማካፈል የምናገኘው ነው። ይህም መጠነ ራብዒት ይባላል።ይህም የአንዱ ወንጌላዊ ድርሻ ማለት ነው። በዚህም መሠረት ቀሪው አንድ ከሆነ ዘመኑ ማቴዎስ ሁለት ከሆነ ዘመነ ማርቆስ ሦስት ከሆነ ዘመነ ሉቃስ ምንም ቀሪ ባይኖር ደግሞ ዘመነ ዮሐንስ ነው።

ቀመሩም ወንጌላዊ
=ዓመተ ምሕረት + ዓመተ ኩነኔ ሲካፈል ለአራት
=1999 +5500 ሲካፈል ለአራት
= 7499 ሲካፈል ለአራት
=1874 ደርሶ ቀሪ 3 ነው።
ይህም የአንዱ ወንጌላዊ ድርሻ 1874 ደርሶ ቀሪ 3 ይሆናል። በቀመሩ መሠረት ቀሪው 3 ስለሆነ ዘመኑ ሉቃስ መሆኑን እንረዳለን።
mÆÒ /mSkrM 1/Ý
መባቻን ለማወቅ ዓመተ ዓለምን ከመጠነ ራብዒት ጋር ደምሮ ለሰባቱ ዕለታት አካፍሎ ቀሪው አንድ ከሆነ መባቻው ማክሰኞ ይሆናል፡ ቀሪው ሁለት ከሆነ ረብዕ ቀሪው ሦስት ከሆነ ሐሙስ፡ ቀሪው አራት ከሆነ ዓርብ፡ ቀሪው አምስት ከ ሆነ ቅዳሜ ቀሪው ስድስት ከሆነ እሑድ ይሆናል። ያለ ቀሪ ቢካፈል መባቻ ሰኞ ይሆናል። በዚህ መሠረት የ1999 መባቻን ስናሰላ
=7499+1874 ሲካፈል ለሰባት= 9373
= 9373 ሲካፈል ለሰባት=1339 ቀሪ ዜሮ ይሆናል።

ቀሪው ዜሮ ስለሆነ የ1999 መባቻ ሰኞ ይውላል።

የወንበር አወጣጥ፡

የወንበር አወጣጥ ዓመተ ዓለምን ለ19 ዓመት አካፍሎ ከቀሪው ላይ አንድን ለዘመነ አትቶ /ሐሰጥቶ/ የሚገኘው ወንበር ወጣ ይባላል። ወንበር ከአንድ እስከ 19 ድረስ የሚጓዝ የዘመን መስፈርት ነው። አገልግሎቱም አበቅቴንና መጥቅዕን ለማውጣት የሚያገለግል ቀመር ነው።
ወንበር፡
= ዓመተ ዓለም ሲካፈል ለ19 ከቀሪው ላይ አንድ መቀነስ / ለዘመን መስጠት/
በዚህ መሠረት የ1999 ዓ.ም ወንበር
=7499 ሲካፈል ለ19 =394 ቀሪ 13
ከቀሪው አንድ መቀነስ / 13-1/ =12 ወንበር ወጣ ይባላል።

አበቅቴ፡

አበቅቴ ማለት የዘመን ቁጥር ወይም ተረፈ ዘመን ማለት ነው። ቃሉ ከዮናኒ /ግሪክ/ የተገኘ ነው። የፀሐይ ዐውደ ዓመት 365 የጨረቃ ዐውደ ዓመት 354 ዕለት ነው። ፀሐይ ዑደቷን /ጉዞዋን/ ሳትጨርስ ጨረቃ ዑደቷን ጨርሳ እንደገና የተጓዘችው ልዩነት አበቅቴ ይባላል። /365 354 11/ ይህ ተረፈ ዘመን ወይም አበቅቴ ይባላል።

በሌላ መንገድ ደግሞ አበቅቴን ለማግኘት ድሜጥሮስ ከሌሊቱ 23 ሱባዔ ገባ። በሰባት ቢያበዙት 161 ይሆናል። ይህን በአምስት 30 /150/ ቢገድፉት /ቢያካፍሉት/ ቀሪው11 ይሆናል። ይህን አበቅቴ ይሁንህ ብሎታል።

የአበቅቴ መደብ 11 ነው። ከመስከረም እስከ ነሐሴ በሚገኙ 12 ወራት ውስጥ ጨረቃ የሁለት ወር ብርሃን ከመስጠት ጉድለት /ሕፀፅ/ የምታሳይባቸው ስድስት ቀናቶች ይገኛሉ። በዚህ ሥር ቀኑንና ሌሊቱን የምንቆጥርባቸው ሠርቀ ሌሊትና ሠርቀ ወርኅ የሚባሉ መሥፈሪያዎች ይገኛሉ። አበቅቴን ለማግኘት ወንበር በ11 ተባዝቶ ከሠለሳ ቢበልጥ ትርፉ ከሠላሳ ቢያንስ የተገኘው ቁጥር አበቅቴ ነው።
አበቅቴ 11X12 ሲካፈል 30=132
=132 በ30 ቢገድፉት /ቢያካፍሉት/= 4 ደርሶ ቀሪ 12 ይሆናል።
አበቅቴው 12 ይሆናል ማለት ነው ።

መቅጥዕ፡

መጥቅዕ ማለት ደወል የአዋጅ መንገሪያ ነጋሪት ነው። ደወል በተደወለ ጊዜ ተማሪ ወደ ክፍሉ እንደሚሰበሰብ ሁሉ መጥቅዕም አጽዋማትንና በዓላትን ይሰበስባልና። በዚሁ ክፍል አጽዋማትና በዓላት ይታወጃል። ዘሌ. 23:4 ፡ኢዩ.2:15 መጥቀዕ የሚውልበትን ዕለት መሠረት በማድረግ ለበዓላትና ለአጽዋማት ማውጫነት እንጠቀማለን። መጥቅዕ ከ14 በላይ ሲሆን በዓለ መጥቅዕ በመስከረም ወር ይውላል። ከ14 በታች ከሆነ ግን በዓለ መጥቅዕ በጥቅምት ወር ይውላል። በዓለ መጥቅዕ በሁለቱ ወሮች ብቻ ነው የሚውለው።መቅጥዕን ለማግኘት ወንበርን በ19 አባዝተን ለ30 በማካፈል እንቀምራለን።

መጥቅዕ፡ ወንበር X19 ሲካፈል ለ30 ይሆናል።ማለትም፡
የ1999 ዓ.ም መጥቅዕ፡ 12X19 = 228 በ30 ሲካፈል= 7 ደርሶ ቀሪ 18 ይሆናል።የ1999 ዓ.ም መጥቅዕ 18 ነው። መጥቅዕ ከ14 በላይ ከሆነ በመስከረም ከ14 በታች ከሆነ ግን በጥቅምት ወር ይውላል። መጥቀዕ በሁለቱ ወሮች ብቻ ነው የሚውለው።

ተውሳክ፡

ተውሳክ ማለት ጭማሪ ማለት ነው። በዓላቱ የማውለብትን ለማወቅ ከመጥቅዕ ጋር እየተጨመረ የሚቆጠር ነው። ሁለት ዓይነት የተውሳክ አቆጣጠር አለ።

1. የዕለታት ተውሳክ በቅዳሜ ይጀምራል ። የዕለታት ተውሳክን ለማግኘት ከመጥቅዕ ሐኒታ እስከ ነነዌ እስከ ዋለችበት እየቆጠሩ በ30 እየገደፉ /እያካፈሉ/ ቀሪውን በመያዝ ተውሳክ ዕለት ይገኛል።

2. የአጽዋማትና የበዓላት ተውሳክ፡ መሠረታቸው ነነዌ ነው። ከነነዌ ጀምምረን አጽዋማቱና በዓላቱ እስከ ዋሉበት ነው የምንቆጥረው ። ከነነዌ እስከ ዐቢይ ጾም 14 ቀን ፡ እስከ ደብረ ዘይት 41 ቀን ነው።41ን በ30 እየገደፉ /እያካፈሉ/ቢገድፉት ትርፉን ከመጥቅዕ ጋር እየደመሩ የሚውሉበትን ቀን እናገኛለን።

ከነነዌ ጀምሮ ያሉ በዓላትና አጽዋማት እንዴት ይገኛሉ?

መባጃ ሐመር በሚል መጠሪያ የማታወቀው የነነዌ ጾም የሚገባበት ቀን ከዓመት ዓመት ይለያያል። እነዚያን ቀኖች ብንመረምራቸው ከጥር 17 በታች አይወርዱም። ከየካቲተ 21 በላይ አይወጡም። በዓለ መጥቅዕ በመስከረም ሲሆን ጾመ ነነዌ በጥር ወር ትውላለች። በዓለ መጥቅዕ በጥቅምት ከዋለ ጾመ ነነዌ በየካቲት ትውላላለች። ሌሎቹን አጽዋማትና በዓላት ለማወቅ መሠረታችን /መነሻችን/ ነነዌ ነው። ነነዌ ተውሳክ የለውም። መጥቅዕ ከዕለታት ተውሳክ ጋር ተደምሮ ከ30 ቢያንስ የተገኘው ቁጥር ነነዌ ይባላል። መጥቅ ከዋለበት ሳኒታ ጀምረው ነነዌ እስከ ዋለችበት ቀን ስንቆጥር ከ122 እስከ 128 ቀናት ነው የሚሆነው ። ቀመሩም መባጃ ሐመር /ነነዌ/ =መጥቅዕ + የዕለታት ተውሳክ በዚህም መሠረት የ1999 ዓ/ም የነነዌ ጾም መቼ እንደዋለ ለማወቅ ብንፈልግ አሠራሩ፡ መጥቅዕ 18 ነው ። የዋለበት ዕለት ደግሞ ሐሙስ ዕለት ነው። የሐሙሰ ተውሳክ ከላይ እንደተገለጸው 3 ነው ዕለቱን ስንደምራቸው፡

ነነዌ፡

= መጥቅዕ + የዕለታት ተውሳክ
= 18 + 3 /የሐሙስ ተውሳክ/
= 21

በዓለ መጥቅዕ በመስከረም ስለዋለ ነነዌ ጥር 21 ትውላለች። ከዚህ በኋላ ያሉትን አጽዋማትና በዓላት ለማዉጣት ነነዌን ከአጽዋማቱ ወይም ከበዓላቱ ተውሳክ ጋር መደመርና ማግኘት እንችላለን።

ዐቢይ ጾም

= ነነዌ + የዐቢይ ጾም ተውሳክ
= ጥር 21 +14
= 35 /በ30 አካፍለን ቀሪውን እንይዛለን/
= 5

= ዐቢይ ጾም የካቲት 5 ቀን ሰኞ ይውላል።

ደብረዘይት

= ነነዌ+ የደብረ ዘይት ተውሳክ
= ጥር 21 ጭ 11
= 32 / በ30 አካፍለን ቀሪውን እንይዛለን/
= 2

ደብረ ዘይት መጋቢት 2 እሑድ ይውላል።

ሆሣዕና

= ነነዌ+ የሆሣዕና ተውሳክ
= ጥር 21+ 2

= ሆሣዕና መጋቢት 23 እሑድ ይውላል።

ስቅለት

= ነነዌ+ የስቅለት ተውሳክ
= ጥር 21+7
= 28

= ቅስለት መጋቢት 28 ዓርብ ይውላል።

ትንሣኤ

= ነነዌ+ የትንሣኤ ተውሳክ
= ጥር 21+ 9

= 3ዐ
=ትንሣኤ መጋቢት 3ዐ እሑድ ይውላል::

ርክበ ካህናት

= ነነዌ+ ርክበ ካህናት ተውሳክ
= ጥር 21ቄ 3
= 24
= ርክበ ካህናት ሚያዝያ 24 ረቡዕ ይውላል::

ዕርገት

= ነነዌ + የዕርገት ተውሳክ
= ጥር 21+18
= 39 /በ3ዐ አካፍለን ቀሪውን እንይዛለን/
= 9
= ዕርገት ግንቦት 9 ሐሙስ ይውላል::

ጰራቅሊጦስ

= ነነዌ+ የጰራቅሊጦት ተውሳክ
= ጥር 21 +28
= 49 /በ3ዐ አካፍለን ቀሪውን እንይዛለን/
= 19 ጰራቅሊጦስ ግንባት 19 እሑድ ይውላል::

ጾመ ሐዋርያት

= ነነዌ+ ስመ ሐዋርያት ተውሳክ
= ጥር 21 + 29
= 5ዐ /በ3ዐ አካፍለን ቀሪውን እንይዛለን/
= 2ዐ
= ጾመ ሐዋርያት ግንባት 2ዐ ሰኞ ይውላል::

ጾመ ድኅነት

= ነነዌ + ጾመ ድኅነት ተውሳክ
= ጥር 21 +1
= 22
= ጾመ ድኅነት ግንቦት 22 ረቡዕ ይውላል::

የ1999 ዓ.ምየ ዘመነ ሉቃስ የበዓላትና የአጽዋማት ማውጫ ከዚህ እንደሚከተለው ነው::

አጽዋማትና	በዓላት	የሚውለበት	ቀንና	ዕለት
መባቻ-	መስከረም	1		ሰኞ
ጾመ	ነነዌ-	ጥር	21	ሰኞ
ዐቢይ	ጾም-	የካቲት	5	ሰኞ
ድበረ	ዘይት-	መጋቢት	2	እሑድ
ሆሣዕና	-	መጋቢት	23	እሑድ
ስቅለት-		መጋቢት	28	ዓርብ
ትንሣኤ-		መጋቢት	3ዐ	እሑድ
ርክበ	ካህናት-	ሚያዝያ	24	ረቡዕ
ዕርገት-		ግንቦት	9	ሐሙስ

ጰራቅሊጦስ- ግንቦት 19 እሑድ

ርእሰ ዐውደ ዓመት

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የመሸጋገሪያው ዕለት በየዓመቱ ቅዱስ ዮሐንስ እየተባለ ይጠራል:: ርእሰ ዐውደ ዓመት በግዕዝ ሲሆን በአማርኛ የዘመን መለወጫ ቅዱስ ዮሐንስ እንቁጣጣሽ እየተባለ ይጠ

ራል። ይህ በዓል የዓመት መጀመሪያ እንደ መሆኑ መጠን ለአውራጎም ጥንታቸው ነውና በየ ዓመቱ በወሮች በመጀመሪያ ቀን ይከበራል።

ርእሰ ዐውደ ዓመት መስከረም አንድ ቀን ለምን ይከበራልሕ በኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ በመስከረም ወር የሆነበትን ምክንያት ሊቃውንቱ ሲያትቱ ብርሃናትሐ ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብትሐ የዓመት ዑደታቸውን በጓጉሜን ጨርሰው በመስከረም ወር ስለሚጀምሩ ነው። ያን ጊዜ ሌሊቱም ከቀኑ ጋር ይተካከላል። ዓመቱንም ጠንቅቀው ሲቆጥሩት 364 ይሆናል። ለዘመን መታወቂያው ይሆን ዘንድ ፀሐይና ጨረቃ ከዋክብትን ፈጠረ ይላልና። ሔኖክ 21: 49። በሌላ በኩልም በዘመነ ኖህ ዓለምን ውኃ አጥለቅልቋት ከቆየ በሁዋላ ዳግመኛ ከነበረው ውኃ የተገለጠችበት ወር ነው። ኩፋ 7: 1። በመጀመሪያው ወር ምድር ታየች የንፍር ውኃም ከምድር ደረቀ የሚለውን መሠረት አድርገው የአቡሻኽር ሊቃውንት የዘመን መለወጫን ታሪካዊ አመጣጥ ያስቀምጣሉ።

የቤተ ክርስቲያኒቱን ቀኖናዊ ሥርዓት ጥናት ያደረጉ አበው ረእሰ ዐውደ ዓመት መስከረም አንድ ቀን መሆኑን አስመልክተው በክታባቸው እንዳስፋፉት አራቱ ወንጌላውያን ዘመኑን እየተካፈሉ በዮሐንስ ተጸንሶ ሚበዘመነ ማቴዎስ ተወልዶአል። በዘመነ ማርቆስ ተጠምቋል በዘመነ ሉቃስ ተሰቅሎ ዓለምን ከፍዳና ከመርገም ነፃ አውጥታል እያሉ ታሪካዊ ሐረጋቸውን ተከትለው ያለ እንቅፋት እንደሚጓዙ ያስረዳሉ።

ቅዱስ ዮሐንስ ርእሰ ዐውደ ዓመት ለምን ተባለ?

ቅዱስ ማርቆስ ወንጌሉን ሲጽፍ የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ወንጌል መጀመሪያ እነሆ መንገድህን የሚጠርግ መልዕክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ። የጌታን መንገድ አዘጋጁ። ጥርጊያውንም አቅኑ። እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ ተብሎ በኢሳይያስ እንደተነገረ የነቢዩ ዘካርያስ ልጅ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በዘመነ ብሉይ መጨረሻና በዘመነ ሐዲስ መጀመሪያ ላይ ተነስቶ መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ስለ ክርስቶስ አዳኝነት እየመሰከረ በምድረ በዳ የንስሐን ጥምቀት እያጠመቀ ለኃጢአት ሥርየት እየሰበከ መጣ ብሎ ለዘመነ ወንጌል የመጀመሪያ ምዕራፍ እንዳደረገው ይታያል።ማር 1:14 ኢሳ40:3-4።

የመጥምቁ ዮሐንስ ተግባር ለዘመነ ወንጌል በር ወይም መነሻ ሆኖ መገኘቱን በመረዳት የቤተ ክርስቲያን አበው የበዓላትን ድንጋጌ በወሰኑበት አንቀጽ የመጥምቁ ዮሐንስ መታሰቢያ በዓል የኢትዮጵያ ርእሰ ዐውደ ዓመት በሚሆን መስከረም አንድ ቀን እንዲከበር በየ ዓመቱ የዘመኑ መጀመሪያ በእርሱ ስም እንዲጠራ አደረጉ / ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ገጽ 1-3/።

የዘመን አቆጣጠራችን ከምዕራባውያን ለምን ተለየ?

ኘሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ባሕረ ሐሳብ በሚለው መጽሐፋቸው የኢትዮጵ ያ ዘመን አቆጣጠር ከምዕራባውያን የተለየበትን ሲያትቱ ዋናዉ ነገር አንድ ታላቅ ታሪካዊ ድርጊት ፈልጎ እርሱን መነሻ ማድረግ ነው።ሮማውያን የሮም ከተማ የተቆረቆረችበትን ዘመን መነሻ አድርገውት ነበር። ታላቁ እስክንድርም የገነነበት ዘመን መቁጠሪያ ሆኖ ነበር። የእኛ ካህናትም ዛዘመነ እስክንድርዛ በሚል ስም ይጠቀሙበት እንደነበር መጻሕፍት ይመሰክራሉ። ሶርያውያን ፣ የዘመን አቆጣጠር ማለት በፀሐይ ቆጥሮ ለዓመቱ 365/6 ዕለት መስጠትን ከሮማውያን በተዋሱ ጊዜ የዓመቱን መጀመሪያ ርእሰ ዐውደ ዓመት ይባላል። ጥቅምት/ቅቸተጸበጽረ 1/ ቀን ላይ አድረገውት ነበር። በኋላ የስማዕታት መታሰቢያ እንዲሆን በ460 ዓመተ እግዚእ ወደ መስከረም/ስጽፕተጽመበጽረ 1/ ቀን ለወጡት ። ግብጾችና እኛ ርእሰ ዐውደ ዓመታችን መስከረም አንድ ቀን ያደረግነው ይኸንን በመከተል ነው። የዓመቱን መጀመሪያ በመስከረም ማድረግን ከሶርያውያንም ሆነ ከግብጾች ብናገኘውም ጀማሪው በ46 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ይገዛ የነበረው ዩልዮስ ቄሣር ስለነበረ በዩልዮስ ባሕረ ሐሳብ /ጅጭለፀቷነ ቸቷለቷነደጽረ/ ይባላል።

ዩልዮስ ቄሣር በ46 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ባወጣው የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት መሠረት ዓመቱን 365 ዕለተ ከ6 ሰዓት አድረጎ ለአራቱ ወሮች 30፣30 ዕለት ለአንዱ 28 ወይም 29 ዕለት ለቀሩት ሰባት ወሮች 31፣31 ዕለት መድቦላቸው 12 ቦታ ከፍሎታል። ይህም 12 ወሮች መሆናቸው ነው። እኛ በዓመቱ ቀኖች ተስማምተን በወር ስንከፍል ተለያይተናል። ዋናው ነገር ዓመቱ ውስጥ ባሉት ዕለቶች መስማማታችን ነው። ይላሉ።

አሥራት ገብረ ማርያም የዘመን አቆጣጠር በሚለው መጽሐፋቸው እንደገለጹት ዲዮናስዮስ የተባለው የሮማ መነኩሴ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ተወለደባት ዘመን በስሌት ለመድረስ የተከተለው መንገድ የታሪክ ክስተትን ነበር። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ዘመን ለመወሰን የታሪክ ክስተትን አልተከተለችም።እርስዋ የተከተለችው ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን የ5500 ዘመንን ነው። ይህንን አባባል ሲያረጋግጡ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ እንዲህ ብለዋል፣ ኢትዮጵያ ዘመነ ብሉይን እንዲህ አስተካክላ 5500 ብላ ስትቆጥር ዘመነ ሐዲስ ልዩ ሆኖ ከማንም ቁጥር አይገጥምም። ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ከምስራቆቹም ከምዕራቦቹም ሁል ጊዜ በሰባት ዓመት ታጎድላለች።ምክንያቱም ባለ ታሪኮችን ትታ ወንጌል ተርጓሚዎችን ትከተላለች ብለዋል በዚህም መሠረት የኢትዮጵያና የአውሮውያን የዘመነ አቆጣጠር ልዩነት ሊኖር የቻለው።

ይህ ልዩነቱም ኢትዮጵያ በመጻሕፍት ትርጎሜ መሠረት መነሻዋ የ5500 ዘመነ ፍጻሜ ሲሆን አውሮውያን ግን መነሻ ያደረጉት የታሪክ ክስተትን በመሆኑ ነው።

ማጎበረ ቅዱሳን